# ርዕዮተ-ዓለም

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሊህቆች ዘንዳ በተለይም ደግሞ የአንድነትና ብሔራዊ ኃይል ተብሎ መጠራት ከሚሻው የሚወረወረው ፀረ-ርዮተዓለም ፀረ-ድርጅት ኢ- ዴሞክራሲያዊ ነገድ በተቋዋሚው ጎራው ከአንድነትና ከሕብረት ይልቅ ክፍፍሉ የበዛው በትግል ግብ በኃይል አሰላለፍ ወዳጅና ጠላትን ለይቶ አስፈላጊውን መስዋእትነት ለመክፈል አለመፈለጉ ብቻ ሳይሆን ችግሩ የሚከተሉትን ርዕዮት እንኳን በውል ያለመገንዘብና እምነታችን ነው የሚሉትን እሴት የማጣትና የዳበሳ ጉዞ በመሆኑ ነው። ይኸው ሊህቅ የፖለቲካ አንድነትና ሕብረትን እውን ለማድረግ ርዕዮት፤ ድርጅት፤ የዴሞክራሲ ጥያቄ ደንቃራ ናቸው ሲል ያማርራል። ለዚህም በስልሳዎቹ የተጀመረውን የግራውን እንቅስቃሴ ጧት ማታ እየከሰሰ ውሎ ያድራል። ብዙዎቹ ግራ ቀመስ ድርጅቶች የደረሰቡት የማይታወቅ ቢሆንም የዚሁ የግራ እንቅስቃሴ ውጤትና በፅናትም ቆሞ የሚገኘው ድርጅት ኢሕአፓ በመሆኑ የኩነናው ሰለባ ሁኖ ቆይቷል። መንስኤውም ከሕዝብ በስተጀርባ የሚደረገውን ኢ- ዴሞክራሲያዊ በባዕድ የተደገፈን ሴራ ሁሉ እየተከታተለ የዴሞክራሲ ቁማራቸውንና ሀገርና ሕዝብን ተገን ያላደረገ የሥልጣን "የለማኝ ለማኝ ቆሮንጮዬን ቀማኝ" ገበናቸውን አደባባይ እያወጣ ሰለሚያጋልጣቸው ብቻ ነው።

ርዕዮተ-ዓለም ሲባል ኮሙኒዝም ይመስለን ይሆን? በአብዛኛው ርዕዮት አስፈላጊ አይደለም የሚሉት ጉምቱ የፖለቲካ ሊህቆች የተማሩ በመሆናቸው፤ መማር ለመመራመር እንጂ ደንቁሮ ለማደንቆርም እንዳይሆን በርግጥ ርዕዮት፤ ዴሞክራሲና ድርጅትስ ምንድን ነው? ታሪካዊ አመጣጡስ እንዴት ነው? በአገራችንስ ነበረ ወይ ለምንድንና እንዴትስ? መቼስ ተጀመረ? ብለን እንድንጠይቅ ግድ ነው። እንዲህ ዓይነት ክርክሮችን በትክክል እንድንረዳ የርዕዮት ትርጉሙን አብራርቶ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው፡፤ ርዕዮቶችንም ጠንቅቆ ማወቅም አስፈላጊና ከፖለቲካ ብዥታና አባቶቻችን የከፈሉትን ክቡር የሕይወት መስዋእትነት የብሔራዊ አርበኝነትን ዋጋ በማጣጣል $500 ዶላር አምጡ የአርበኝንት ሠነድ ትሸከፋላችሁ ከሚሉን የፖለቲካ ነጋዴዎች እንዴት ለምን ብለን በመጠየቅ ሳናውቅ ስህተት ከመፈፀም ያድነናል። የዚህ ፅሁፍ ትኩረትም የፖለቲካ ርዕዮትን ማዕከል ያደረገ ይሆናል።

ዘመናዊ ርዕዮቶች ቅርፅ እየያዙ የመጡት በግምት ከ1600 እስከ 1800 በዘመነ መነቃቃት ሲሆን(*enlightenment*) በተከተታይ ምዕተ-ዓመት ባገኙት ተቀባይነትና በተሰጣቸው ትኩረት፤

በኃሏም በነ አይዛክ ኒውተን የዓለመ ራዕይ ሥርዓተ ተፈጥሮ (*vision of universal order*) በደስካርተስ የአመክኗዊ ጥርጣሬ(*rationalistic skepticism*) በፍራንሲስ ባኮን የተሞክሮ ቀዳማይነት (*empiricism*) ዓለምን የመገንዘብና የማስረዳት እይታ በመቀስቀስና በመነሳሳት፤ የመነቃቃት አራማጆች አየጎለበቱና እየደረጁ መጥተዋል።እነዚህም የመነቃቃት አቀንቃኞችና አራማጆች በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ እጅጉን የማይስማሙና የተለያዩ አመለካከቶች የነበራቸው ቢሆንም ቅሉ፤ ግና ደግሞ ሦስት የኅብረተስብ ዋና ጠላቶች የገባር ሥርዓት፤(*feudalism*) የመንግሥት ንዋየ (ንግድ) ቁጥጥርና (*mercantilism*) የሃይማኖት ቀኖና ናቸው ሲሉ ይስማማሉ፡፡

አዲሱ ርዕዮትም የማህበራዊ ከበሬታንና ቦታን በኮንትራት ፤ቀኖናን በሳይንስ ፤የመንግሥት ንዋየ (ንግድ) ቁጥጥርን ደግሞ በውድድር የሚተካ በመሆኑ የዘመኑ ነጋዴዎች ፤ የኢንዱስትሪና የፋይናንስ ባለሀብቶች ያረጁ ጠላቶች ናቸው በሚሉአቸው ንጉሣዊያን፤ መኳንንትና ካህናት ላይ ለሚያካሂዱት ጥቃት ምክንያትና ዋቢ (*justification* ) ሰለሆናቸው መነቃቃትን ወዲያው ተቀበለው ተግባራዊ አድርገውታል ። የመጨረሻ ውጤቱም መልካም የተፋጠነ የምጣኔ ሀብት እድገትና የኅብረተስብን ቁሳዊ አቅም ያዳበረና ያስፋፉ በርዕዮተዓለም የተደገፈ የካፒታሊስት ሥርዓት እውን መሆን ነበር።

በታሪክ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ሊህቃን ብቻ ሳይሆኑ በአውሮጳና በአሜሪካም የነበሩና ያሉ፤ ርዕዮት ፋይዳ ያለው ጉዳይና ለውይይትም የሚበቃ አይደለም፤ ያሉና የሚሉ ሊህቃን በየጊዜው አልጠፉም፤ ግና ደግሞ ርዕዮተዓልም አቸናፊ ሆኖ እስካዛሬ ድረስ ዘልቋል። ትኩረትም እንደነፈጉት ርዕዮት ትርጉሙ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይህ ፅሁፍ ባደረገው የአሰሳ ጥረት የኮሎምቢያ፤ የካቶሊክና የብርታኒካ ኢንሳይክሎፒድያ በቂ ዝርዝር የነፈጉት ቢሆንም ቅሉ ርዕዮተዓለምብብብብብብብብብብብብብብ በኮሊየርስ ኢንሣይክሎፒዲያ *Collier's encyclopedia* ትርጉሙን "IDEOLOGY": the science dealing with beliefs, notions, and

theories growing out of fundamental assumptions held by a group; also, the sum of such beliefs, notions, and theories. Acceptance of ideology and being conditioned by it are requirements for membership in groups. Sometimes such indoctrination is conscious; often it is informal. Sometimes the member makes a conscious effort to acquire the right ideas; more often he accepts them unconsciously. Further, since a person may belong to more than one group, it is possible for him to hold conflicting ideologies. Thus one may hold to a religious belief in the brotherhood of man and, at the same time, hold that an elite manage affairs with a minimum of attention to the desires of minority groups. Implicit in the idea of ideology is the theory that what one believes will vary with time and place and that opinions must be interpreted in terms of group allegiance. This leads to a philosophy based on cultural conditioning

The concept of ideology arose in Europe as a result of a conflict of various systems of thought. It has found use as a means of discounting the arguments of an opponent as reflecting merely his preconception or prejudices. Thus Marx argued that much religious and political thinking was ideological and served to protect capitalism." እንዲህ ሰፍሮ ይገኛል።

ስለሆነም ርዕዮተዓለም ባህልን የተጎዳኘ፤(*culture bound*)የኅብረተሰብ ዓቢይ እቶች(*values*)ስብስብና ጥንቅር(*constellations*) ሲሆን ፤እሴቶችም ሰብእ እጅጉን አስፈላጊ በሆኑ የፓለቲካ የምጣኔ ሀብት ማህበራዊ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት ወይንም ደግሞ መደምደምያ የሚደረስባቸው መስፈርቶች ናቸው ፡፡ ርዕዮተ-ዓለም በተለይ በፖለቲካው ረገድ የተወሰኑ ግቦች የሃሳብ ስብስብ ና አጠቃላይ ራዕይ (*comprehensive vision*) ነው።

ርዕዮተዓለም የምጣኔ ሀብት የማህበራዊ ይሁን የፖለቲካ ፍልስፍና ዓቢይ ሁነው የሚጠነጠኑበት ቀመር ነው፡፡ ዓለምንም የመመልከቻ፤ የመተርጎሚያና የመለወጫም፤ የሃሳብ ዘዴ (*system of*

*ideas*)ነው። ርዕዮትም ለመሠረታዊ የእሴት ጥያቄዎች መልስ መስጫ አጠቃላይና በምርምር የጠራ(*comprehensive coherent process* )ፈለግ ነው።

ለምሳሌ ፡ እኛ ማነን? ለምንስ ይህን እናደርጋለን? እኔ እንዴት ሕይወቴንና ኅብረተሰቤን ከራሴና ከሌሎች ጋር ያለኝን ቁርኝነትና ግኙኝነትስ እንዴት መግለፅና ማስረዳት እችላለሁኝ? የፓለቲካ ሰውነቶች ወይንም የፓለቲካ ድርጅቶች ደግሞ የራሳቸውን ድርጅት ማንነትና ሕጋዊነት (*legitimacy of their organization*) እንዲሁም የራሳቸው ሚና (*legitimacy of their role*) የሚወሰነው በርዕዮት በተቀኙ ስነ አመክኗዊ( *belief system s rationalized by ideology*) እምነቶች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚገድ በመሆኑ ርዕዮት እንዴት እንደሚቀረፅና እንዴትስ ደግሞ እንደሚተረጎም ማወቅን ልዩ ትኩረት ቢሰጡትና እንደየአመለካከታቸውም የሚከተሉት ርዕዮት ቢኖራቸው የሚደንቅ ሊሆን አይገባም፡፡ በዚህም ምክንያት ርዕዮቶች ሁሉ እያንዳንዱ የኅብረተሰብ ክፍል እንደየአመለካከቱ በኅብረተሰቡ ውስጥ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ መስጫ ቁስ ሁኖ ሲያገለግሉት ቆይተዋል ።

ለምሳሌ፤ እንዴት ለምን ብለን ራሳችንን እንጠይቅ።
ለምን አስጸያፊው ግለስባዊነት ይወደሳል፤ ይሞገሳል?
ከገበያ ውድድር ለምን የመንግሥት እቅድ ምጣኔ ሀብት ይመረጣል?
ከብዙኃኑ ጥቅም ይልቅ እንዴት የግል ጥቅም ይቀድማል?
የመንግሥትንስ በማህበራዊ አግልግሎት በስፋት የመሳተፉን ጉዳይ ለምን እንቃወማለን?
በመንግሥት አውቃቀር ረገድስ የሕግ መወሰኛው ሥልጣን ለምን ይገደባል?
የሕግ አስፈጻሚው አካል ሥልጣንስ ለምን መገደብ የለበትም?
በፖለቲካዊ አስተዳደር መዋቅርም እንዴት ከበሐርታዊ (ፌደራላዊ) አድያማት፤ የጎጥ (ፌደራላዊ)አድያማት ይመረጣሉ?... ወዘተ እያልን ብንመረምር አዕምሮአችን ሊያደራው የሚቻለው ሆልቆ መሳፍርት ነው።

ይህ ዝርዝር አመልካች እንጂ ዝርዝሩ በዚህ የሚያበቃና የሚቆም አይደለም፡፡ ከላይ ለምንዘረዝራቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች የምንሰጣቸው መልሶች በጋራ ማህበራዊ ተሞክሮአችን ላይ ተንተርሰው በእምነትና በምርምር በተደገፈ አስተሳሰብ የሚቀረፁና የሚገለፁ ሲሆኑ አንዳንዴም እነዚህ መልሶች አግባብነት የጎደላቸው ኢ- አመክኗዊና ኢ-ታሪካዊ(*illogical and ahistorical*) ቢሆኑ የሚገርም አይደለም። በጥቅሉ(*in the aggregate*) መልሶቹ በየዘርፉ መቅረባቸው አግባብና አግባብነታቸውም አንድ የተለየና የተወሰነ ቡድን የሚያምንበት ዐቢይ የርዕዮተ ዓለሙ ተግባር መገለጫ በመሆናቸው ነው። ርዕዮት ቀመስ ክርክሮች ልዩነት መፍጠራቸው አሌ የሚባል ሀቅ አይደለም። ችግሩ የርዕዮቶች መኖር ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ ነፃነት ሰፍኖ ርዕዮተኞችም ለዴሞክራሲያዊ እሴቶችና ለምልዓተ ሕዝቡም ይሁንታ መገዛት መቻሉ ላይ ነው።

ርዕዮቶችም ሁሉ ከባህል የተጎዳኙ(*culture bound*) አንዳንዴም ርስ በራስ የሚጣረሱ አራት ጠቃሚ ተግባራትን፤

ሀ. ገዢ ተቋማትንና መደብን ለመንከባከብ ፤

ለ. ግለሰብንና ማህበረሰብን ለጋራ ዓላማ ለማሰለፍ፤

ሐ. የተወሰኑ እሴቶችን ብቻ የገሀዱ ዓለም አጠቃላይ አመለካከት ዘለዓለማዊ አድርጎ ለማቅረብ፤

መ. የማደናገሪያም (*mystification*) መሣርያ በመሆን፤ ለማገልገል ይውላሉ። ከዚህም ባሻገር ርዕዮት፤ተቋማትን፤ የተቋማትን ሚና፤ ሥልጣንና ኃላፊነትን ከያዙት ደግሞ፤ ምንድን መጠበቅ እንዳለብን ይነግረናል።

በኅብረተሰቡ ዘንዳ ማናቸውም ዐቢይ ጉዳዮች የሚቀረፁት በርዕዮተዓለም በመሆኑ እያንዳንዱ ቡድን እሴቴ ናቸው በሚላቸው እንዲሁም በተለያዩ የፓለቲካ የምጣኔ ሀብት የማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ፖሊሲ ነክ ክርክሮች ርዕዮታዊ ቃና ያላቸው ይሆናሉ። በተለያዩ የፓሊሲ ነክ ጉዳዮች ላይም አለመግባባት ሲፈጠር ርዕዮት ራሱን ከቃላት እሰጥ እገባ አልፎ ልዩነት በመፍጠር ወደ ጠብ መሣሪያነት የሚሸጋገርበት ጊዜም ይኖራል ፡፡ በተለይም በአሁኑ ጊዜ አንዱ ርዕዮት ሌላውን ለማቸነፍ የሚያደርገው ትንንቅ አስፈሪና ከፋፋይ ቢመስልም መሠረታዊ የዴሞክራሲ መብቶች ከሰፈኑና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችም እልባት ካገኙ ርዕዮት ከፋፋይ ሳይሆን የሃብና የፖሊሲ

አማራጭ ብቻ ይሆናል። ከቀኝ እስከ ግራ የምንይዘው ርዕዮት መሰረቱ ዴሞክራሲያዊ እሴቶች ናቸውና ዴሞክራሲያዊ እሴቶች የሚጎሉትን የጎጠኝነት ርዕዮትም ለመታገል ብርታት ከመሆኑም በላይ ፤ ከዘርና ከጎጥ ጠባብ አመለካከትና ከፍፍልም ወጥተን የዓለም-እይታ (world view) አድማሳችንን እንድናሰፋ ይረዳናል።

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ እጅግ የሚገርመው በአንድ ወቅት "ተራማጅ" ማርክሳዊ ርዕዮት አነገብን ያሉ ገሚሱ በባዕድ ርዳታ ለሥልጣን የበቁ የፖለቲካ ሊህቃን "ተራማጅ " ጭንብላቸው ወልቆ በምዕተ-ዓመታት በሚቆጠር የጊዜ መዘውር ወደ ኃላ መልሰውን በጎጥ የብረት ዘንግ የቁም ስቅል ያሳዩናል። ገሚሱም ለሥልጣን ያልበቃው " የነፃነት፤የእኩልነት፤ የዴሞክራሲ ታጋይ" የምኩራብ ፀሎታቸውን አብቅተው በሚገርም ፍጥነት በየጎጡ በዘር መደየናቸውንና መደበራቸውን ስናይ ወትሮም የምኩራቡ የዴሞክራሲ ፀሎታቸው ከግብዝነት ያለፈ እንዳልነበር ፀሐይ የሞቀውና የቅስፈት እንደነበር የሚታወቅ ነው። እነዚህ የፖለቲካ ኩማሪቶች አዳፍነው ያሉት ርዕዮትና በተነው ያሉት ድርጅትም ተግዳሮቶችን (challenges) ሁሉ አቸንፎ ለእሴቱ ለሕዝብና ለሀገር ጥቅም በዓይነትና በጥራት በፅናት ዋርዲያ ቆሞ ሲያዩት ትንቢታቸው ስላልያዘና ፤ ያሰቡት ባለመከወኑም፤ ጀርባቸውን ቀዝቃዛ ላብ ኸር ብሎ ሲያርሰው እየደነገጡ የፖለቲካ ትግሉን ሕግ ለመቀየር ርዕዮትንና ድርጅትን ምክንያት አድርገው ኢሕአፓን ይከሳሉ።

ዛሬ የምናደርጋቸው ማናቸውም ርዕዮተ ቀመስ ክርክሮች ከቀኝና ከግራ ዝንባሌ የዘለሉ አይደሉም። ግና ደግሞ አሰላለፉ በተለይ በፖሊስ ነክ ጉዳዮች ላይ በንዑሳን መስመሮች በአቋም ቢለይ ክርክሮችን ወደ መሀል መስመር እያቀራረቡ በመተማመን አሊያም በድምፅ እየተሸናነፉ ዴሞክራሲያዊ ሂደትን ከማደርጀት የሚያግዱ ሀገርንም የሚከፋፍሉ አይሆኑም፤ የፖለቲካ መረጋጋትንም ያሰፍናሉ።

ርዕዮተ ዓለም የተግባር ዋቢና ማስረጃ በመሆኑ፤ ለድርጅቶች ተቀባይነትን ፤እንዲሁም በቅራኔዎች መሀከልም ርቅን መፈለጊያ ቁስ ነው። ያለ ርዕዮት ኅብረተሰብ ፤ግለሰቦችም ይሁኑ ድርጅቶች ምንድን ማድረግ እንዳለባቸው የሚናገርቡትን ልሳንን ያጡ ይሆናሉ፡፡ ርዕዮት አስፈላጊ አይደለም ብለን የምንከራከር ከሆነ ችግሮች ባጋጠሙን ጊዜ መፍቻ እሴቶች እየጠፉን ግለሰቦች ተቋማትና ኅብረተሰብም ሽባ ይሆናሉ ወይንም ተዓሚነት የጎደለው ውሳኔና ድንጋጌ ይከተላል፤ ሕዝብና

ሀገርም ይጎዳል፡፡ በግልም ይሁን በቡድን እሴቶቻችን ናቸው የምንላቸውን አጥብቆ መያዙ አስፈላጊ ነው። ሀገርና ሕዝብን በተመለከተ ከምንለያይባቸው ጉዳዮች ይልቅ የምንገናኝባቸው ይበልጣሉና አንድነቶቻችንን ነቅሶ አውጥቶ በእነርሱ ዙሪያ መሰለፍ ሀገሬ ለሚል ዜጋ ሁሉ እጅጉን ወሳኝ ነው።

ርዕዮት በራሱ በውስጡ በውጥረት የተሞላ ቢሆንም በግልም ይሁን በቡድን እሴቶቻችን ናቸው የምንላቸው እምነቶች ከሌሉን በኅብረተሰቡ ለሚነሱ የፖለቲካ የምጣኔ ሀብትና ማህበራዊ ጥያቄዎች መልስ እየጠፋን መደናገር ይመጣል፤ ወዳጅና ጠላትንም ለመለዬትያስቸግራል። ርዕዮት ውሳኔ ሰጭዋችንና ድንጋጌ አፍላቂዋችን ከስህተት ይከላከላል፡፡ ርዕዮት አስፈላጊነቱ በተለይ የፓለቲካ የሃይማኖት የምጣኔ ሀብት፤ አንዳንዴም ርስ በራስ የሚቃረኑ ጉዳዮችን ለማስታረቅ ይውላል ። የሰዎችን መሠረታዊ የሆኑ ፍላጎቶቻቸውን ደህንነታቸውንና ዋስትናቸውን እያረጋገጠ ሰዎች እንዴትና ለምን መሠረታዊ በሆኑ ሀሳቦች በመግባባትና በመተሳሰር እንዴትስ ደግሞ ማኅበረሰብን በእምነትና በፍቅር መገንባት እንደሚቻላቸው መርህ በመሆንም ግዙፍ ሚና ይጫወታል። ይህም ከቀኝ እስከ ግራ የርዕዮተዓለም ፅንፍ የምንከተለውን ቡድኖች ሁሉ የሚያካትትና የሚያስተባብር ሊሆን ይችላል። ቁም ነገሩ ካለንበት ጊዜና ቦታ ነባራዊና ውስብስብ ሀገራዊው ኩነታን አገናዝቦ ትክክለኛው መልስ ላይ መድረስ መቻሉና የሀሳብና የፖሊሲ አማራጮችንም አቅርቦ በሕዝብ ይሁንታ መከወን ነው። ሰለሆነም እያንዳንዱ ኅብረተሰብም የግድ ርዕዮተዓለም ያሰፈልገዋል ፡፡


ኢትዮጵያ ከዚህ ውጪ ልዩ ሊያደርጋት የሚችል አንዳችም በቂ ምክንያት የለም፡፡ በኢትዮጵያ አብዛኛው የኅብረተሰባችን እሴት በሰነድ የተዘገበ ሳይሆን በቃል ከትውልድ ትውልድ በብሂል፤ በትውፊትና በአፈ ታሪክ እየተላለፈ የቆዬ ሲሆን፤ ዛሬም በአብዛኛው በሠነድ የተዘገበውም በፍትኃ-ነገሥት ስለነገሥታቱ፤ በቤተክህነትም በአማልክት ገድል ዙሪያ መሆኑ ፤ ዘመናዊ ትምህርት ሲጀመርም በግብረገብነት፤ በታሪክና ምሳሌ ከዚያም አልፎ በልብ ወለድ መልክ የሥርዓቱን ክፋትና ደግነት፤ፍትሃዊነትና ፍርደ-ገምድልነት ለማጋለጥ የሞከሩ የወገንና የሀገር ፍቅርንም ለማስተማር የተደረሱ የታሪክ፤ የትምህርትና የሀይማኖት ድራሳናት ከሀሳብ አልፈው፤ በርዕዮት ደረጃ ከአውሮጳ መነቃቃትም ትምህርት ቀስመው በርዕዮት ደረጃ ሊቀረፁና ሊደራጁ አልቻሉም። እንደኢትዮያዊው ፈላስፋ ዘርዓ ያዕቆብ በዘመኑ የተነሱ ሊቃውንት የመኳንንቱን አኗኗርና የቄሳውስቱን ትምህርት መመርመርና መጠየቅ ሲጀምሩ ዕጣ ፈንታቸው ግዞትና ስደት ነበር።

ኅብረተሰባችን የሌላውን የኅብረተሰብ ሥርዓት መኖር ሳያውቅ ለምሳሌ፤ ባሪያ ማሳደርን፤ የገባር ሥርዓትን መተዳደሪያው አድርጎ ኖሯል፤ በኢትዮጵያ የባሪያ ሥርዓትና የገባር ሥርዓት ሀገር በቀል ነው። የገባር ሥርዓት ለምን የኅብረተሰብ እድገት ሕግን ተከትሎ ወደ ካፓታሊዝም አላደገም ሰፊ ጥናትን ይጠይቃል። በአንድ ጊዜና ቦታ ድንቅ የግንባታ ቅርሶችን ለታሪክና ለዓለም ሕዝብ የተወ፤ ትላልቅ ከተሞችን ለመገንባት ምንድን አገደው? አውደ-ነገሥትን (የኮከብ ቆጠራን)፤ የቀን መቁጠሪያን የቀመረ፤ ድንቅ የሥዕልና የሙዚቃ ጥበብን፤ ሥርዓተ- ፅህፈትን ያደራጀ ሕዝብ ምን ያህል በራሱ ጊዜና ቦታ አዕምሮውን በማሠልጠን የአዕምሮ ችሎታውን ለመጠቀምና ለማዳበር ያደረገውን ጥረትና ስኬት ስናይ ይህ እድገት ለምን ተገታ? ብለን መጠየቃችን አልቀረም፤ መልስም የሚሻ ነው። በአጠቃላይ ይህ ፅሁፍከአሥራ ሦስተኛው ክፍለ

ዘመን አንስቶ በተከታታይ (በግራኝ መሀመድ፣በገባሩ ሥዓርትና በወል (*egalitarian*) ነገዳዊ

ማህበረሰቦች፣ በዘመነ መሳፍንት) በተደረጉ ጦርነቶች አንዱ ወገን ፍፁም አቸንፎ መውጣት አለመቻሉ፣ (በ1966 የደረስንበትን የመሬት ስሪት ልብ ይሉዋል) እንዲሁም ኢትዮጵያን ቅኝ ለመግዛት የተደረጉ የውጪ ወረራዎችና ክፍተኛ የመለኮታዊ እምነት ጫና የኅብረተሰብን እድገት በተዋረድ እያጨናገፈው የምርት ኃይሉም በተዋረድ በጊዜውና በቦታው በልማትና ፈጠራ ላይ እንዳያተኩር አድርጎታል ብሎ ያምናል።

ይህ ፅሑፍ የደረስንበትን የሀገራችንን ቀደምትና ዘመናዊ የዓለም አመለካከት ከዚህ በታች በሠሌዳዎች በግርድፉ ለማስቀመጥ ሞክራል። የመሃል ሠሌዳው ባዶ ቢሆን አይገረሙ ቢፈልጉ በቀኝ ወይንም በግራ እሴትዎን እየፈለጉ ሲሻዎ እያሻኮቱ የሚከተሉትን ወይንም ደግሞ መከተል የሚሹትን ርዕዮት ይፈልጉበት። ዛሬ ከቀኝ እስከ ግራ የምንከተላቸው ርዕዮቶች በይዘታቸውና በእሴት ዋጋቸው ከዚህ የዘለሉ አይደሉም። ግና ደግሞ ይህን ለመረዳት የሰከነ ሀገር በቀል የፖለቲካ ሳይንስን ተገን ያደረገ ትንተናን ግድ ይላል።




ዘመናዊ የዓለም አመለካከት ከቀደምት አመለካከቶች ጋር እያነፃፀሩ ራስን እንደግለሰብ ና እንድቡድን ከኅብረተሰብ ጋር እያጎዳኙ ከነዚህም በግልና በቡድን እንደየአመላካከታችን የምናምንባቸውን የፖለቲካ ፍልስፍና ትንተና ብንሰጠው ከቀኝ ርዕዮት እስከ ግራ ርዕዮት አንዱን እንደወገንን ማወቅ ይቻላል።

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ማኅበራዊ እሴቶች አጠቃላይ ገሀደ-ዓለም (*universal*) መሆናቸውን ነው።

በዓለም የተቀነቀኑ ዛሬም እየተቀነቀኑ ያሉ የፖለቲካ ርዕዮቶች ከካፒታሊዝም እስከ ኮሙኒዝም ወይንም ከሊበራል ዴሞክራሲ እስከ አብዮታዊ(ማዕከላዊ) ዴሞክራሲ ያሉት ናቸው።

ኢትዮጵያውያን ዓለምን የሚመለከቱበት እሳቤ እንደነበራቸው ከላይ በግርድፍ የተቀመጠውን ብሂልና ተውፊትን ይመለከቱዋል። ቀደምት ኢትዮጵያዊያን ሊቃውንት ፤"ደብተራዋቹ" ምንም እንኳን በተለያየ ዘመን ነገሥታቱን ቢተቹና ቢነቅፉም ሀሳባቸው ከቤተክህነት አልፎ መንግሥትን የመቅረፅና ሥልጣኑንም የመወሰን ሕዝቡንም ከባርነት ወደ ነፃነት የሚያሸጋግር ሆኖ አልተገኘም፡፡ከውጭ ርዕዮት ለመቅሰምም ግኙኝነታቸው ከግብፅና ከኢየሩሳሌም ያለፈ አልነበረም፡፡ ቤተክርስቲያንም በግብፅ ኮፕቲኮች ተፅዕኖ ሥር ጳጳስ ሳይቀር እያስመጣች ከእስክንድሪያ ቁጥጥርም ለመላቀቅ ብዙ ዘመን ፈጅቶባታል። ዘመናዊ ሥልጣኔንና የጊዜውንም ተክኖሎጂ ለማስገባት ከውስጥ ቤተክርስቲያንና መኳንንቱ ከውጪ ደግሞ የባዕዳን እቀባ በዘመኑ ደንቃራ ሁኖ እንደቆዬ ታሪክ የዘገበው ነው።

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ፍለጋ ጥረት የተጀመረው ከዘመነ መሳፍንት ጦርነት ማለቂያ በኃላ በአፄ ቴዎድሮስ ሥርወ-መንግሥት ሲሆን፤ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥትም በጊዜውና በቦታው በጥራትና በዓይነት አድጎ የታዬ ሲሆን ይህም ጥረት በቀ. ኃ. ሥ. የቀጠለ ቢሆንም የኅብረተሰቡን የልማት ፍላጎት ለማሟላት የመኳንንቱንና የገባር ሥርዓቱን ይሁንታ ሊያገኝ አልቻለም።

በኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ቤተክህነት ሰምና ወርቅ ሆነው መቆየታቸው ይታያል፡፡ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኃላም በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ በአጭር የተቀጨው ዘመናዊ ትምህርት በቀ.ኃ. ሥ. ዘመነ መንግሥት እየተስፋፋ የመጣ ቢሆንም ቅሉ ውጤቱ የቤተክህነቱን የሥራ ድርሻና ሚና በመሻማቱ ፍትጊያ መጀመሩ አልቀረም፡፡ ፊውዳላዊው ሥርዓትና መኳንንቱ ዘመናዊ ሥልጣኔን በጀ ብሎ ሊፈቅድ የሚቻለው አልሆነም ፡፡ነጋዴ መጫኛ ነካሽ የእጅ ባለሙያው ሸማኔ፤አንጥረኛ፤ሸክላ ሥራ፤ቆዳ ፋቂ እየተበለ የሥራ ዘርፍና የሥራ ክፍፍሉ በመናቁ፤ ሙያውም ከቤተሰብ ዙሪያ አልፎ በኅብረተሰቡ ዘንዳ በብዛትና በጥራት በመስፋፋት የኅብረተሰቡን የቁስ ጥያቄ በሚማላትና ሀገራዊ ም ገበያ በመፍጠር ለኅህብረተሰብ እድገት አስተዋፅኦ ማድረግና ኅብረተሰቡንም መቀየር በሚችል ደረጃ ማደግ አልቻሉም።

በዘመኑም በአገር ውስጥና በውጭ አገር ዕውቀትን የገበዩት ሊህቃን መሠረት የሌላቸውና በራሳቸውም ኅብረተሰብ ውስጥ የተጫወቱትና የሚጫወቱት ማህበራዊ ሚና ያልነበራቸው፤ በግል ምኞት ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ስነ- ልቡናቸውም የሸማች እንጂ የአምራችና የልማት አልነበረም። ምሁራኑ በቀሰሙት ትምህርት ዞግ ያገኙት ድሎትና ምኞት ተስማምቶአቸው በምንዱባን ከተማ

የባለፀጋውያን ደሴት ሰርተው ራሳቸውን ከኅብረተሰቡ አግልለው ኖረዋል።   በየካቲት  አብዮት ለአሥለጠናቸው  ካፐታሊዝም  በክፉ  ቀንም  ላስተማሩዋቸው ንጉሥም  ውለታ  መክፈል  አልቻሉም፤ በተቋም  ደረጃም  ራሳቸውን  ለማደራጀት  ያልታደሉ  ከመሆናቸው  ባሻገር  እንደቤተክህነት  ሁሉ ከዘወዱ  ጋር  ሰምና  ወርቅ  ሆነው  ከመቆየታቸውም  በላይ  በዙፋኑ  ላይ  የተነሳውን  ማናቸውንም የሥልጣን  ፤ የሙብትና የፍትህ  ጥያቄ  አደገኛ  ነው  ሲሉ  አምርረው  ታግለዋል፡፡እነዚህም ሊህቆች ዛሬ ርዕዮት ድርጅት ደንቃራ ነው ቢሉን የደሙ ደም የገዢው መደብ ከማለት በስተቀር ምንድን ገላጭ ቃል ይገኛል?

የፊውዶ-ቡርዣው  ሥርዓት  በቅራኔ  ላይ  የተገነባ  በመሆኑ  የርዕዮት  ይዘቱ  በአንድ  በኩል  ፊውዳላዊ በሌላ  በኩል  ደግሞ  ካፒታሊዝም  መሆኑ  አልቀረም  ፡፡ይኸም  በታሪክ  ተቃራኒ  የነበሩ  ሁለት ሥርዓቶች  በአንድ  ጊዜና  ቦታ  ላይ  ተጣምረው  እንዲታዩ  ግድ  ብሏል።  የቡርዣው  ርዕዮት  ዘመናዊ ትምህርትን ተገን አድርጎ የገባ እንደመሆኑ ከሥራ ክፍፍልና ከንግድ የተገኘውን ንዋየ ክምችት ለልማት በማዋል አምራችና አልሚ ኃይል አልነበረም። በምትኩ በመኳንንቱ አሮጌ ካባ እየቀና ደጃዝማችና ቀኛዝማች ለመባል የንጉሡን ጫማ የሚስም እንጂ የካፒታል ስልተ ምርትን ማደራጀት ካለመቻሉም በላይ፤ ብቅ ብቅ እያለ ለመጣው የነጋዴ ቡርዣ እንኳን አጋር መሆን አልቻለም። በዚህም ቀጣዩ ትውልድም ከአንጋፋዎቹ ይህ ነው የሚባል ተሞክሮ አልጠበቀውም። ያ ትውልድ ወደ ግራ እንዲያዘንብል ግድ ካሉት ምክንያቶች አንዱ ምክንያት ይህ ነበር ሲል ይህ ፅሁፍ ያምናል።

መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄዎችን በማንሳት የተነሳው የመምህራን የተማሪውና የሠራተኛውእንቅስቃሴ ወደ ግራ ርዕዮት እንዲያዘነብል ግድ ካሉት ከላይ የተጠቀሱት ሀገራዊ ኩነታዎች ሲሆኑ፤ ከዓለም አቀፍ ኩነታዎች ደግሞ ሥልጣኔ ባዘመነው አውሮጳ እንደ ዛሩ ሩሲያ እጅግ ኃላ ቀር ሀገር  በአጭር ጊዜ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መጥቀው ኃያል መንግሥት መሆናቸው በሩቅ ምስራቅ  ኮሙኒስት ቻይናና ኢምፔሪያል ጃፓን ከኢትዮጵያ ያልተሻሉ ፍፁም ፊውዳላዊ ሀገሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ረሃብና ቸነፈረን አስወግደው በሳይንስና ቴክኒሎጂ መራቀቃቸው በተቃራኒው ደግሞ በምዕራብ አውሮጳ ከፓሪስ ኮሚዩን አንስቶ እስከ አሜሪካ አብዮት ድረስ ነፃነት እኩልነትና ፍትህን በየሕገ መንግሥታቸው አስፍረው ሕጉን ሲያከብሩና ለሕጉም ሲገዙ ግና ደግሞ የነፃነት የእኩልነትና የፍትህ  መተክላቸውን በመፃረር የቅኝ አገዛዝ መስርተው በተለይም በደቡብ አፍሪካ አፓርቴይድን በሀገራቸውም ውስጥ በአሜሪካ የዘር መድሎን በጀ ማለታቸው በ60ዎቹ የነፃነት የእኩልነትና የፍትህ  እንቅስቃሴዎች ዓለምአቀፍ ይዘትም ተፅእኖ አድርጎ እንደነበር ማጤኑ ተገቢ ነው። በ60ዎቹ እየተጠናከረ የመጣው ግራ ዝንበሌ በአጭር ጊዜ ውስጥ

ወገናችንን ከረሃብ ጠኔ ከርዛትና ደዌ ነፃ አውጥተን በሚል እምነት እንጂ ለባዕድ የፖለቲካ ፍልስፍና ሀይማኖትና ባህልም ራሱን አሳልፎ የሰጠና ያጎበደደ አልነበረም። ምንም እንኳን የግራ ዝንባሌ ቢኖረውም ኢትዮአያዊነትን ማዕከሉ አድርጎና አጥብቆ የያዘ ብሔርተኛም ነበር ማለት ይቻላል።

ርዕዮትን ጠብ ጫሪ እያደረጉ መሠረታዊ ለውጥን መከላከል ለውጥም አብዮታዊ ርዕዮትም አመፅ ነውና መቅረት አለበት፤ ማለት የሕዝቡን ትግል ትጥቅ ማስፈታት ነው።ይህ አመለካከት የዚያው የገለማው የፊዩዶ-ቡርዣ አስተሳሰብና ለከት የለሽ የፖለቲካ ኩማሪቶች ብቻ ነው። ለራሳችን የምንመኘውን መልካም ነገር ሁሉ ለወገናችንም ብንመኝ ብሩህ ተስፋ ብሩህ ራዕይ እንጂ ጨለምተኝነት ባይሆን እንዴት መልካም ነበር።

ርዕዮታቸውን አፅንተው የያዙትን መቀየር አለባቸው የሚሉም አልጠፉም። ምን አዲስ ነገር ተገኝቶ ተብለው ሲጠየቁ መልስ የላቸውም። ራስን አለመቀየር የአዕምሮ ጤንነት አይደለም እስከማለት የደረሱም አሉ። የአዕምሮ በሽተኞችስ ምንም እንኳን ቢማሩና ቢራቀቁ የአዕምሮአቸውን የማሰብ ችሎታ መጠቀምና አዕምሮአቸውን ማሰልጠን ያልቻሉ ዛሬ ለደረሱበት የኢኮኖሚም ይሁን የዕውቀት ልዕልና ጥገቶቹን እየሸጠ ያስተማራቸውን ሕዝብ ገበና በምርምር ስም እየነገዱበት፡ ቅኝ ሊገዙን በጀ ያላልናቸውና ያሳፈርናቸው ጠላቶቻችን፡ በታሪክ አቂመው እየተበቀሉን መሆናቸውን መረዳት ያቃታቸው ግብዞች ብቻ ናቸው። ዛሬም ካፒታሊዝም እጅጉን የገለማ ለመሆኑ ዓለም አቀፍ የምጣኔ ሀብት ድቀቱ ገሀድ አድርጎ እያሳየን ነው። እኮ ምን አይተን እንቀየር? የሚያምኑበትን እሴት በፅናት ይዞ ሕይወትንም እምነትንም መኖር መቻል፤ በህዝብና በሀገርም ላይም ደባ ከመፈፀም መቆጠብ ትልቅ ፀጋ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ልሂቃንን ልዩ ፀባይ የሚሰጠን ማርክሳዊ ስንሆን ማን ከእኛ በላይ እረ ማን ደርሶ ማርክሲስት? ሊበራል ነን ስንል ማን ከእኛ በላይ ሌበራልማለታችን ነው። አንድ ዓይነት ርዕዮትም፤ የምንጋራው እሴትም እያለን መግባባት አለመቻላችን የሚገርም ነው። በሕዝባዊ ትግሉ ዘንዳ ትብብር የጠፋው ሀገርና ሕዝብ ከማጥ ገብቶ የሚገኘው በርዕዮት መከፋፈል ብቻ ሳይሆን ርዕዮታችን ምን እንደሆነ ሳናውቅ በሀገርና በሕዝብ ብሶት ስም የሚያደናግሩንን በግልብ ስለምንከተል ብቻ ነው፡፡ አንድ ዓይነት ርዕዮትም እየተከተልን በትንሹ እንኳን እሴታችን ነው በምንለው መግባባት እያቃተን እኔስ ከማን አንሼ በሚል ፈሊጥከሀገርና ከሕዝብ ይልቅ የራስ ዝና በልጦብን የፖለቲካ ውርዴ እየመታን የቆየው የምንከተለውን ርዕዮት ትርጉም እንኳን በውል አለማወቃችንና ብዙውን ጊዜም የምናባክነው ያሉንን ልዩነቶች አንጥሮ በማውጣት፤ መስማማት በሚቻልባቸው የጋራ ግንዛቤ እየጨበጡ በልዩነቶች ላይ ደግሞ አንዱ የሌላውን የሃሳብ ነፃነት በማክበር አመለካከታችንን የምናራምድበትን ኩነታ መፍጠሩ ላይ ሳይሆን በተለያዩ መንገዶች አንዱ ሌላውን በመጥለፍና በማዳከሙ ላይ መሆኑ ነው።

አባቶቻችን ያልጨረሱትና በአደራ የተውልንን የአንድ ኢትዮጵያን ብሔራዊና ሕዝባዊ መንግሥት የመገንባት የትውልድ ግዴታ ለመወጣት፤እያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅት የራሱ የሆነ ርዕዮተ ዓለም ሊኖረው ይገባል። የፖለቲካ ድርጅቶች አንድነትና ሕብረትንም ከመፍጠር በፊት የራስን የፖለቲካ የምጣኔ ሀብትና ማህበራዊ የፖሊሲ አቋም በግልፅ ማስቀመጥን የሌሎችንም የፖለቲካ ድርጅቶች አቋም በሚገባ ማወቅንም ግድ ይላል። የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፤ የምጣኔ ሀብትና ማህበራዊ ችግሮች እጅጉን ውስብስብ በመሆናቸው ሊታረቁ የማይችሉ አመለካከቶችን በውል አውቆ ማክበርን፤ ሊታረቁ የሚችሉትን ደግሞ ከራስ አቋም ጋር አቀራርቦ ትብብራችን ለማይቀረው የኢትዮጵያ ብሔራዊና ሕዝባዊ መንግሥት እውን መሆን አበክሮ በትጋት መታገል እንጂ "ርዕዮትና ድርጅት ዴሞክራሲ አስፈላጊ አይደሉም" የሚል ዳፍንት የፖለቲካ ትንተና የአንድነትና የሕዝባዊ ትግሉን ትጥቅ አስፈቺ ከመሆኑም በላይ በሕዝብ ላይ የተቃጣ ከፍተኛ ደባና የባዕዳንም የታሪክ በቀል ሴራ አካል ነው።

ታደሠ ተስፋዬ (ቆሪጥ)

tadeqorit@aol.com May 23, 2009